የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 61
ADDIS ABABA 11th August, 2014

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፰፻፷፫/፪ሺ፮ ዓ.ም

የሰንደቅ ዓላማ (ማሻሻያ) አዋጅ ..............ገጽ ፯ሺ፬፻፹፩

**CONTENTS**

Proclamation No. 863/2014

Flag /Amendment/ Proclamation ...................Page 7481

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፷፫/፪ሺ፮

## የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፬/፪ሺ፩ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፬/፪ሺ፩ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሰንደቅ ዓላማ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፰፻፷፫/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ማሻሻያ**

፩/ የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፬/፪ሺ፩ አንቀጽ ፬ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፬ ተተክቷል፡-

"፬. **የሰንደቅ ዓላማ ቀን**

ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን (ከዚህ በኋላ "ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን" እየተባለ የሚጠራ) በየዓመቱ ጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሰኞ በአገር አቀፍ ደረጃ ይከበራል፡፡"

## PROCLAMATION No. 863/2014

## A PROCLAMATION TO AMEND THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA FLAG PROCLAMATION No. 654/2009

WHEREAS, it has been found necessary to amend the Flag Proclamation No. 654/2009;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as "Flag /Amendment/ Proclamation No.863/2014."

2. **Amendment**

1/ Article 4 of the Flag Proclamation No. 654/2009 is deleted and replaced by the following new Article 4:

"4. **The Flag Day**

The National Flag day /hereinafter "the National Flag Day" / shall be celebrated at national level every year on the first Monday of the Ethiopian month of Tikimit.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፬/፪ሺ፩ በአንቀፅ ፳፪ ከንዑስ አንቀፅ (፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተጨመረ ሲሆን ንዑስ አንቀፅ (፫) እና (፬) የነበሩት እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀፅ (፬) እና (፭) በመሆን ተሸጋሽገዋል፡-

"፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በስራ ላይ በማይሆንበት ጊዜ ብሔራዊ የሃዘን ቀንና ሰንደቅ ዓላማው ዝቅ ብሎ የሚውለበለብባቸው ሁኔታዎች በምክር ቤቱ አፈጉባዔ የሚወሰን ይሆናል፡፡"

፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2/ the following new sub-article (3) is added after sub article (2) of Article 22 of Proclamation No. 654/2009 and Article 22 (3) and (4) are renumbered as (4) and (5):

"3/ Notwithstanding the provision of sub article (2) of this Article when the House of Peoples' Representatives is in recess, the Speaker of the House may declare half-masting and a national mourning day."

3. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter in to force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of August, 2014**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ